# ለከ ኃይል

ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም አሜን

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ
የግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ

ትርጉም
ዲያቆን ማለደ ዋስይሁን

2005 ዓም

www.ethiopianorthodox.org

©ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻፬ ዓ.ም

[illegible]
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

[illegible]

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

[illegible]

E-mail: lemat@eotc-mkidusan.org
Wbesite:- www.eotc-mkidusan.org



# ይዘት

ሰሙነ ሕማማቱን የማሰብ አስፈላጊነት ........ 1
የሰሙነ ሕማማት ሥርዓቶች ........ 9
መከራ መስቀሉ እንዴት ተጀመረ ........ 16
ጸሎተ ፍትሐት ........ 22
ከሠፈሩ ውጪ ........ 29

የሰሙነ ሕማማት መዝሙር ........ 34
ምሥጢራዊው አዲሱ የኃይል እሳቤ ........ 50
ለከ ኃይል ........ 58
ሞትን ለመቀበል በተዘጋጀ ጊዜም ኃያል ነበር ........ 68
በተያዘ ጊዜም ኃያል ነበር ........ 77
ለፍርድ በተመረመረም ጊዜ ኃያል ነበር ........ 85
በስቅለቱ ጊዜም ኃያል ነበር ........ 96
በሞቱም ጊዜ ኃያል ነበር ........ 102
ከሞቱም በኋላ ኃያል ነበር ........ 110

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኃይሉን ከዲያብሎስ ሰወረ......................118

ክብርም የአንተ ነው........................................125

‹‹የተናቀ በሰዎችም የተጠላ››......................133

አንተ ክቡር አምላካችን ነህ....................143

አሁንም ዳግመኛ እናከብርሃለን...................152

በረከትና ቅድስናም ሁሉ የአንተ ነው................162

ልዕልናም ሁሉ የአንተ ነው..............................179

ለከ ኃይል



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

www.ethiopianorthodox.org

# ሰሙነ ሕማማቱን የማሰብ አስፈላጊነት

ሰሙነ ሕማማት በየዓመቱ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ጥልቅ መንፈሳዊነት የሚታይበት ሰሙን ነው፡፡ የድኅነታችንን እጅግ በጣም ወሳኝ የሆነውን ደረጃ በድኅነታችንም ታሪክ የላቀውን ምዕራፍ በጥልቅ የምናስብበት ሳምንት ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ሳምንት ከብሉያትና ከሐዲሳት የተውጣጡ፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለና የነበረውን ግንኙነት የሚያብራሩ የተወሰኑ ምንባባትን መርጣ ታዘጋጃለች፡፡





www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ እጅግ ጥልቅ ስሜት የሚፈጥሩ ዝማሬና ተመስጦ ታቀርባለች፡፡

በመጀመሪያዎቹ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን አባቶቻችን ሳምንቱን እጅግ ታላቅ በሆነ ክብርና መገዛት እንዲሁም በጥልቅ ስሜት ይቀበሉት ነበር፡፡ ሲጾሙም የጌታችንን መከራ በማሰብ ውስጥ ልንቀምሳቸው የማይገቡ ጣፋጮች ከማንኛውም ዓይነት ቅብና ስብ እንዲሁም ማርን ከመሰሉ የሳሙ የጣሙ ምግቦች ተከልክለው ይጾሙ ነበር፡፡

አንዳንዶች ፈጽሞ ምግብን አያበስሉም ነበር፤ ከምግብ ተከልክለው ይጾሙ ነበር፤ ምግብን ማዘጋጀት በጊዜው ሊያደርጉ ከሚገባቸው ትጋትና መገዛት እንዳያቦዝናቸው ያስቡ ነበርና፡፡ አብዛኛዎቹም ክርስቲያኖች ከኅብስትና ከጨው በስተቀር ሌላ አይመገቡም ነበር፡፡ እንዲሁም በግብጽ ቤተክርስቲያን ትውፊት መሠረት ደግሞ አቅም ያላቸው ሁሉ ከዓርብ ምሽት ጀምሮ ትንሣኤው እስከሚበሠርበት ዕለተ እሑድ ጠዋት ድረስ ከምግብ ራሳቸውን ይከለክሉ ነበር፡፡

የሳምንቱ ታላቅነትና የትጋት ጊዜ የመሆኑ ምልክት ሴቶች ጌጥና መዋቢያ ከማድረግ ከመጠቀም ይቆጠቡ እንደነበር ሲታወስ ነው፡፡ ሰዎችም ሁሉ ጊዜያቸውን ለትጋት ለጌታችንም ክብር ያውሉት ነበር፡፡ በቤተ ክርስቲያን ለጸሎትና ለተመስጦ ይሰበሰባሉ፡፡





ታላቁ ንጉሥ ቴዎዶስዮስ በዚህ ወቅት መንግሥታዊም ሆነ ሌሎች ሥራዎች ሁሉ ቆመው በሥርዓተ አምልኮው በመመሰጥ ማሳለፍ እንዲቻል ያዝዙ ከነበሩ ክርስቲያን ነገሥታት አንዱ ነበር፡፡ ለመታረም ራሳቸውን ለማነጽ ይጠቀማቸዋል ተብሎ ተስፋ ስለሚደረግ እስረኞች ጭምር ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሔዱ በሥነ ሥርዓቶቹም ላይ እንዲገኙ ይፈቀድ ነበር፡፡

ክርስቲያን ጌቶችም በባሮቻቸው ላይ ልዩነት ሳይፈጥሩ ከየትኛውም ሥራ ተቆጥበው እንደ ጌቶቻቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስቡት ዘንድ በዚህ ሰሙን ያሳርፏቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ጌቶችና ባሮች ሁለቱም በዚህ ሰሞን ለጌታ ይገዙ ነበር፤ የዚህን ሳምንት ጥልቅ መንፈሳዊ በረከትም ይሳተፉ ነበር፡፡

## የሰሙነ ሕማማት ሥርዓቶች

በዚህ ሳምንት ቤተ ክርስቲያን የምታተኩርበት ዋናና ብቸኛ አሳብ አንድ ነው፤ የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ፡፡ በዚህም ምክንያት የሚደገሙ መዝሙራት፣ የሥርዓተ ጸሎት ሰዓታት፣ ከጌታችን ጋር የተዛመዱ የተለያዩ ጉዳዮችን ማለትም ልደቱንና፣ አገልግሎቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዕርገቱን፣ በአባቱም ቀኝ መቀመጡን፣ ዳግመኛም በክብር የሚገለጥበትን

www.ethiopianorthodox.org

# መከራ መስቀሉ እንዴት ተጀመረ?

በዕለተ ሆሳዕና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ንጉሥ አቀባበል ወደ ተደረገለት ቦታ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ሕዝቡም አመስገኑት፤ ዘመሩለት፤ ዘንባባ ይዘው፣ ልብሳቸውንም በእግሮቹ ሥር አንጥፈው ደስታቸውን ገለጹ። ከተማውም ሁሉ ታወከ (ማቴ 21፥10)። ይህም ሊቃነ ካህናቱን የሕዝቡንም ሽማግሌዎች ጸሐፍት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንን አስቆጣ።

ሕዝብ ስለ እርሱ ባደረበት የፍቅር ስሜት ለሰጡትም ታላቅ ክብር ቀኑበት። ስለዚህ ያስወግዱት ዘንድ ማሰብ ጀመሩ። ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ፣ በዚያ የነበሩትን ሻጭና ገዢዎችን ገሥጾ ባስወጣ ጊዜ እጅግ ክፉኛ ተቆጡ።

ከዚህም ‹‹አንድስ እንኳ ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን እነሆ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሔዷል›› አሉ።/ዮሐ 12፥19/። ‹‹በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ?›› ሲሉ ጠየቁ /ማቴ 21፥23/።

ሊቃነ ካህናቱ ካደረባቸው ክፉ ቅናት የተነሣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይገድሉት ዘንድ ፈለጉ። አስገራሚው እንቆቅልሽ ግን የተከተሉት ሰዎች /ሕዝብ/ ያደረባቸው





ዝንባሌ /የአቋም ለውጥ/ ነው። እንደ ንጉሥ ይቀበሉት ዘንድ የዘመሩለት እነሱ ኋላ ደግሞ "ስቀለው፣ ስቀለው!" እያሉ ሲጮኹ ተገኝተዋልና /ሉቃ 23፥21/።

ሕዝቡ ቀድሞም እንደ ንጉሥ ሊቀበሉት የወደዱት ምድራዊ ንጉሡ መስሏቸው ነበርና ነው። "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት" /ማር 11፥9-10/ አሉ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በምድር ላይ ያለን ንግሥናን ተቃውሟል፤ እርሱ ሰማያዊ ንጉሥ ነውና። ናዝራዊውን ለማስወገድ የተሰለፉበት የሊቀ ካህናቱ ሴራም የሚጠበቅ ነበር፤ እነርሱ ሲጠብቁት በቆዩት ንግሥና /ግዛት/ ተስፋ አጥተው ነበርና።

ቤተ ክርስቲያንም የዕለተ ሆሳዕና ሥነ ሥርዓት ፍፃሜን የሰሙነ ሕማማቱ መጀመሪያ አድርጋ ታስባለች። ጌታችንን ለመግደል ማሰብ የጀመሩት ከዚያች ሰዓት በኋላ ነበርና።

በዚህ ሳምንት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት፣ ዓምዶች፣ አትሮንስ እና አንዳንዴም ግድግዳዎቹም ጭምር በጥቁር ልብስ ይሸፈናሉ። ይህም የሐዘን ድባብን ለመፍጠር ነው። እያንዳንዱም አማኝ በክርስቶስ መከራ የተካፈለ ያህል እንዲሰማው ያደርጋል። ቅዱስ ጳውሎስም "እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰሙነ ሕማማቱ በቅድሚያ የሚመሰገነው ገናናው ኃይሉ ነው። አዎ ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው" /1ቆሮ 1÷24/ እንዳለው ጌታችንን "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም..." እንለዋለን።

እውነት ነው። አንዳንዶች በመስቀል ላይ የደከምህ የተሸነፍህ ይመስላቸዋል፤ ጌታ ሆይ እኛ ግን አንተ ማን እንደ ሆንህ እናውቃለን። አስቀድመን በምናውቀው ኃይልህ አንተ ፈጣሪ መሆንህን ነው። "ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳችስ እንኳ ያለእርሱ አልሆነም" /ዮሐ 1÷3/ አንተ ዳኛ/ፈራጅ/ ሆነህ በክብር በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ የምትመጣበት ኃይል አለህ።

እርግጥ ነው፤ የተሰቀለው ጌታ እንደ ደካማ የመሰላቸው ሰዎች ከእነርሱ ጋር ያሳልፍ በነበረበት ጊዜና በየዕለቱ ያደርግ የነበረውን ቢያስቡት ኖሮ የባሕርይ ኃይል ያለው መሆኑን ባወቁ በተረዱ ነበር። እርሱ በተአምራቱና በቅድስናውም ሁሉ ኃያል ነው።

ጌታ ሆይ! አንተ ብቻ ኃያል ነህ፤ ሌሎች ሁሉ ኃጢአትን ተቋቁመው መገኘት ባልቻሉ ጊዜ "ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፤ እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው" /ምሳ. 7÷26/። በመጽሐፍም





"ሁሉ ዐመፁ፤ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድ ስንኳ የለም" እንደተባለ /መዝ 14÷ 3/ አንተ ግን ኃጢአትን አሸነፍህ።

አንተ አምላኬ ግን አንተ ብቻ ዓለሙን ሁሉ ያሸነፍከው፤ "ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማነው?" /ዮሐ 8÷46/ ያልከው ጌታ ነህ።

አንተ አምላኬ ግን አንተ ብቻ ዲያብሎስን ያሸነፍከው፤ "የዚህ ዓለም ገዢ ይመጣል፤ በእኔ ላይ አንዳች የለውም" /ዮሐ 14÷30/ ያልከው ጌታ ነህ።

አንተ አምላኬ ግን አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ፤ "ቅድስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ ..." /ዕብ 7÷26/ የተባለልህ ነህ።

አንተ አምላኬ ግን አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ፤ "አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ" እያሉ /ራእ 15÷4/ የዘመሩልህ ነህ።

ጌታ ሆይ! ተአምራትህ ያለህን ድንቅ ኃይል ይመሰክራሉ። አንተ "ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው" አደረግህ /ዮሐ 15÷24/። በተፈጥሮም ላይ ያለህ ሥልጣን (ኃይል) ነፋሳትን ማዕበሉንም በገሠጽህ ጊዜ፣ በባሕሩም ላይ በተራመድህ ጊዜ ታይቷልና። ዳዊትም "የባሕርን ኃይል አንተ ትገዛለህ፤ የሞገዱንም መናወጥ ዝም ታሰኛለህ" እያለ ዘመረልህ /መዝ 89÷9/። ለከ



www.ethiopianorthodox.org

# ምሥጢራዊው አዲሱ የኃይል እሳቤ

የዓለም የኃይል እሳቤ ጌታችን ካስተዋወቀን የኃይል እሳቤ የተለየ ነው፡፡ ለዓለም ኃይል ማለት ራስን ተከላክሎ ሌላውን ገዝቶ (አስገዝቶ) የሚኖርበት የመምታት፣ የመግፋት፣ የጠብ የክርክር ኃይል ነው፡፡ ጌታችን ግን አርአያ አድርጐ ያቆመው ኃይል ወሰን የለሽ መውደድን፣ መሥዋዕት የመሆንን፣ የመታገስን ኃይል ነው፡፡

ስለ ኃይል ስናስብ ከቁሳዊ /አካላዊ/ ሳይሆን ከመንፈሳዊ ጐኑ አንጻር እናየዋለን፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችንን ዘወትር በመከራው ውስጥ ትኩር ብለን የምናየው፤ የምናስበው፡፡

ምስኪን ደሀ የሆነው ቁሳዊው ዓለም ግን ጌታችንን ፊቱን በጸፉት፣ በተሳለቁበት፣ ባፌዙበት፣ በሰቀሉትም ጊዜ ሁሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ደከመ ያስባል፡፡ በክርስቶስ ላይ የደረሱበት እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከችሎታ ማጣት የተነሣ ቢሆን ኖሮ የዓለሙ ሐሳብ እውነት በሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ ከእነዚያ ፊቱን ከጸፉት ከሳቁ ከተሳለቁበት፣ ከሰቀሉትም ሁሉ በላይ በእውነት ኃያል ነበር፡፡

እነርሱን ለማጥፋት የሚችልበት የባሕርይ ኃይልና ሥልጣን ባለቤት ነው፡፡ ነገር ግን አላደረገውም፡፡ ይወዳቸዋልና፤



www.ethiopianorthodox.org



ፍቅሩም ከሞት ይልቅ የበረታች ናትና፡፡ እርሱ በሞት ሊቀጣቸው ይቻለው ነበር፤ እርሱ ግን ያን አላደረገም፤ እነርሱንም ከሞት ሊያድን፣ በእርሱም ሞት ሕይወትን ሊሰጣቸው ወደዓለም መጥቷልና፡፡

የጌታችንን ትዕግስቱን እናደንቃለን፤ ‹‹እኛ ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንን ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል፡፡›› ብሎ ሐዋርያው እንደተናገረ ኃይሉ በትዕግስት ውስጥ የተፈጸመ እንደሆነ አሳምኖናል (ሮሜ 15፥1)፡፡

አንዳንድ ሰዎች ለቁጣ የሚያነሣሡ አናሳ ስድብና ንቀቶችን እንኳ ለመታገስ እጅግ ደካሞች ናቸው፡፡ ስለእነዚህ ጥቃቅን ስድብና ንቀቶች ይቆጣሉና፤ ራስን መግዛትን ያሳጣቸዋል፡፡ ወደ በቀልም ያደርሳቸዋል፡፡ ይህም ደካማነታቸውንና የትዕግስትንም ኃይል እንዳጡ ያሳያል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትዕግስቱ ኃያል ነው፡፡ ይህም የፍቅሩን ኃይል ይገልጣል፡፡ ፍቅርም ያለው ማንም ቢሆን ይታገሳል፤ ትዕግስት አለማድረግ ፍፁም ፍቅርን ማጣት ነውና፡፡ ጌታችን በደላችንን ያስወግድ ዘንድ መጣ፤ "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ›› /ኢሳ 53፥6/፡፡

ያለው መሻት (ፈቃድ) ነው፡፡

እርሱ መስቀሉን ለማጥፋት ኃይል አለው፤ እርሱንም ሊሰቅሉት የፈለጉትንም ሁሉ፡፡ ነገር ግን የእርሱ ኃይል ከዚህ ሁሉ ነገር በላይ ታላቅ ነው፤ የፍቅርና የመሥዋዕትነት ኃይል፡፡ እርሱን በመስቀሉ ጉዞ ሁሉ የተከተለው ይህ ኃይል የእኛም ተመስጦ እና እውነተኛ ስሜት ዋነኛ ትኩረት ነው፡፡

## ሞትን ለመቀበል በተዘጋጀ ጊዜ ኃያል ነበር

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በመቀበሉ፣ ወደ ሞትም በመቅረቡ በእውነት ኃያል ነው፡፡ ሰዎች እርሱን በስውር አጥቅተውት ወይም ጎድተውት ወይም በኃይላቸው አስገድደውት የተቀበለው አይደለም፡፡ እንደሚያዝ ያውቅ ነበር፤ ለደቀመዛሙርቱ "ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል" ብሎ እንደነገራቸው ሰዓቲቱንም ያውቅ ነበር /ማቴ 26÷2/፡፡

እርሱ ትክክለኛዋን ሰዓት፣ ቅጽበት፣ ቦታዋንም፣ ወዴትም ሔዶ እንዲይዙት የተቀረጠችውን ሰዓት ያውቃል ብኋል አልተሳሳትንም፡፡



www.ethiopianorthodox.org



የሚያውቃትም ሰዓት በቀረበች ጊዜ በጌቴሴማኒ አንቀላፍተው የነበሩ ደቀመዛሙርቱን ይቀሰቅስ ዘንድ ሔደ፡፡ "እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ እነሆ ሰዓቲቱ ቀርባለች፤ የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል፤ ተነሡ እንሒድ፤ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቧል" አላቸው /ማቴ 26÷45/፡፡

ጠላትም በቀረበ ጊዜ ይገናኘው ዘንድ /ራሱን ይሰጥ ዘንድ/ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደዚያው ቀረበ፡፡ በእርግጥም ራሱንም ስለእኛ ሊሰጥ ፈቀደ፡፡ እንዲህም አለ ‹‹እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም›› /ማር 10÷45/፡፡

## በተያዘ ጊዜም ኃያል ነበር

ኃያሉን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በያዙት ጊዜ ሰይፍና ዱላ ይዘው የመጡት ወታደሮች ፈርተውት ነበር፡፡ እስከ እግረ መስቀሉ የተከተለው ተወዳጅ ደቀመዝሙር ቅዱስ ዮሐንስ ሁኔታውን ሲገልጽ እንዲህ ብሏል ‹‹ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው፤ የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት ኢየሱስ ‹‹እኔ ነኝ›› አለ፡፡ አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር እንግዲህ እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ

ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ›› /ዮሐ 18÷4-5/:: የጌታችን ጠላቶች ወደ ምድር ወደቁ:: እንደ እነርሱ ሰይፍና ዱላ ያልታጠቀ ከእነርሱ የትጥቅ ኃይል ጋር ሊነጻጸር የማይችል ታላቅ ኃይሉን ሊቋቋሙት አልቻሉም::

ጌታችን በዚህ ጊዜ መሰወር ይቻለው ነበር፤ ነገር ግን በዚያ ፋንታ የተረጋጋና ብርቱ ሆኖ ጸና:: እነርሱ ከወደቁበት በተነሡ ጊዜ ጠየቃቸው "ማንን ትፈልጋላችሁ?" አላቸው (ዮሐ 18÷7-9) እነርሱም ‹የናዝሬቱን ኢየሱስን› አሉት፤ ኢየሱስ መልሶ እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደሆናችሁ እነዚህ ይሒዱ ተዉአቸው›› አለ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘ ጊዜ ኃይል የነበረው እንዲህ ሆኖ ነበር:: ሌሎች እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥማቸው ይርዳሉ፤ በጌታችን ዘንድ ግን በተቃራኒው ነበር:: እርሱ የሚፈራ አልነበረም፤ እርሱን ለመያዝ የቀረቡት ግን ፊቱን ለማየት አልተቻላቸውም፤ "እኔ ነኝ" ብሎ ራሱን እስኪያ ቀርብላቸው ድረስ እጅግም ተንቀጥቅጠው ነበር::

ጌታችን በተያዘ ጊዜ ለነበረው ኃይል ሌላው ማሳያ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ጆሮ መፈወሱ ነበር:: "ስምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ስለነበረው መዘዘው የሊቀ ካህናቱንም ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቆረጠ" /ዮሐ 18÷10/:: የሥጋ ኃይል የማይስማማው



www.ethiopianorthodox.org



የዋሁ ጌታችን ወደ ጴጥሮስ ዞር ብሎ ሰይፉን ወደ ሰገባው ይመልስ ዘንድ ጠየቀው:: ራሱን ለመከላከል ሌሎችም ይከላከሉለት ዘንድ አልፈቀደም፤ ቅዱስ ጴጥሮስንም "ሰይፍህን ወደ ሥፍራው መልስ ወይስ አባቴን እንድለምን፤ እርሱም አሁን ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?" ሲል ገሰጸው /ማቴ 26÷53/:: ጌታችን እርሱን ለማዳን የሚደረግ ነገርን ሁሉ ተቃወመ:: ስለ እኛ ድኅነትም ሞትን በታላቅ ብርታት ተቀበለው::

የሊቀ ካህናቱ ባሪያ ጆሮ ሊያዝ /ሊሰቀል/ በቀረበው በእርሱ በኃያሉ ጌታ የተፈወሰ ሆነ /ሉቃ 22÷51/:: ጌታችን ለጠላቶቹ ያለውን ምሕረት (ርኅራኄ) እጅግ ወሳኝ ግሩም ድንቅ በሆነች ሰዓትም አሳይቷል::

እኛም ከእርሱ ከተያዘው ጌታ፣ የባሪያውን ጆሮ ከፈወሰው ጌታ ጐን እንቆማለን:: በተቀደሱ ጆሮዎቹም ""ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም..." እያልን በለሆሳስ እንዘምርለታለን::

ይህ የምሕረት ሥራው ሁሉ በያዙት ወታደሮች፣ አሳልፎ በሰጠው በአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ፣ በመከሩበት በሊቃነ ካህናቱ እፍረትን አሳድሯል:: ይህ በእነርሱም ላይ ምስክር ነው፤ ኋላም እንዲያምኑበት የቀረበ ጥሪ ነው::

ከተያዘም በኋላ በባሮቹ መካከል እንዳለ ንጉሥ ወይም በፍጥረቱ መካከል የሠለጠነ አምላክ ሆኖ ተመላለሰ። ሁሉን ማጥፋት ይቻለው ነበር፤ ነገር ግን የእኛን የሁላችንንም መዳን ወደደ። ኤልያስ ንጉሡን ይገናኘው ዘንድ በጠየቀው በሃምሳ አለቃው ላይ እንዳደረገው ማድረግ ነበር። "ኤልያስም መልሶ የሃምሳ አለቃውን እኔስ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንሁ እሳት ከሰማይ ትውረድ፤ አንተንም ሃምሳውንም ሰዎች ትብላ አለው፤ እሳትም ከሰማይ ወርዳ እርሱንና ሃምሳውን ሰዎቹን በላች" /2 ነገ 1÷10/።

መሲሕ /ክርስቶስ/ በእርግጥም ኤልያስ ያደረገውን በቀላሉ ማድረግ ይችል ነበር፤ እርሱ ግን ሰዎችን ለማጥፋት ሳይሆን ለሰዎች ለመሞት መጥቷልና ያንን አላደረገም። የኃይሉ ፈቃድ በዚያን ጊዜ ራሱን የመግዛት እንጂ እነርሱን የማጥፋት አልበረም። ይህ እኛን ያዳነበት ኃይል ነው፤ ይህ እርሱ ሞትን በታላቅ ብርታት ይቀበል ዘንድ የበቃበት ኃይል ነው።

## ለፍርድ በተመረመረ ጊዜም ኃያል ነበር

ሊቃነ ካህናቱ ፈርተው ነበርና ለፍርድ የመረመሩት በምሽት ነበር። ታውከውም ነበርና "በኢየሱስም ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር፤ አላገኙም፤ ብዙም የሐሰት ምስክሮች





ምንም ቢያቀርቡ አላገኙም" /ማቴ 26÷59/። በእርሱ እርጋታና ዝምታ ተደንቀው ነበር "እነዚህ በሚመሰክሩብህ አንድ ስንኳ አትመልስምን?... ኢየሱስ ግን ዝም አለ" /ማቴ 26÷62-63/።

በክሳቸውና በሐሰት ምስክሮች ጌታችን አልተረበሸም፤ አልታወከምም። ዝምታው ከቃላትም ሁሉ በላይ ኃያል ነበር። ክሳቸውና የሐሰት ምስክርነቱ ረብየለሽ እንደሆነ እንዲሰማቸው አድርጓል። ስለዚህ ሌላ መክሰሻ ይፈልጉ ነበር። እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አድርጎ መናገሩን እንዲቀበል ግድ ይሉት ነበር። ሊቀ ካህናቱም "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ አለው።" በዚህ ጊዜ ግን ዝም ማለት እየተቻለው ነገር ግን በኃይል መለሰላቸው "አንተ አልህ፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ" አላቸው /ማቴ 26÷63-64/።

በጲላጦስ እንዲሁም በቀያፋ ፊትም ቢሆን ኃያል ነበር። ሀገረ ገዢውም "በዚህ ሰው አንድ በደል ስንኳ አላገኘሁበትም"፤ "እነሆም በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም... ለሞት የሚያደርሰው



www.ethiopianorthodox.org

ሁኔታ ላይ ደርሶ ሳለ እንዴት ታላቅ ቃል (ድምፅ) ኖረው? በጌቴሴማኒ ተግቷል፤ ተንገላቷል፤ "ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ" /ሉቃ 22÷45/:: ከዚያም በወታደሮች ተይዟል::

ረጅም ርቀትም በእግሩ ተጓዘ:: በሊቃነ ካህናት ሐናና ቀያፋ፣ በሀገረ ገዢው ጲላጦስ፣ በንጉሥ ሄሮድስ እና ዳግመኛም ወደ ጲላጦስ ለምርመራ (ለፍርድ) አምስት ጊዜ ተልኳል:: ከዚህ በተጨማሪ ድካምና ሊሸከሙት የማይቻል፣ ብዙዎችን ለሞት ሊዳርግ በሚችል ወይም ለሞት ሊያደርሳቸው በሚችል አሰቃቂ የግርፋት ስቀይ ደርሶበታል::

ከመመታቱ በተጨማሪ በእሾኽ አክሊልም ብዙ ደም ፈሰሰው:: እስኪወድቅም ድረስ መስቀሉን ተሸከመ:: "በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት" /ሉቃ 23÷26/::

በመስቀልም ላይ በቸነከሩት ጊዜ የሥጋ ኃይሉም እስኪ ፈስ እጅግ የጸና ስቃይን ታገሰ:: "አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ" የሚለው ቃል ይፈጸም ዘንድም ቆዳው ከአጥንቱ ተጣበቀ (መዝ 22÷17):: ጌታችን ወደ ሞቱ ቅጽበት በደረሰ ጊዜ የቀረለት የሥጋ ኃይል አልነበረም፤ ለሹክሹክታ እንኳ:: ታዲያ እንዴት በታላቅ ቃል (ድምፅ) ጮኸ? ይህቺን ታላቅ የተቀደሰች



www.ethiopianorthodox.org



ቅጽበት በማድነቅ ከእርሱ ጉን እንቆማለን:: "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም..." እያልን እንዘም ርለታለን::

ጌታችን በሞቱ ጊዜ ኃያል ነበር:: ሞትንም በሞቱ አሸነፈ:: የእባቡን ራስ ቀጠቀጠ፤ ለሰው ዘር ሁሉ ከሔዋን ዘመን ጀምሮ የተሰጠው "እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል" የተባለው ቃል ተፈጸመ / ዘፍ 3÷15/:: የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የዓለም መድኃኒት መሆኑን አሳየ::

የጌታችን እጅግ ታላቅ ኃይል ያላት ቅጽበት የሞቱ ቅጽበት ናት:: በዚያች ቅጽበት የሰው ልጆችን ሁሉ በደሙ ገዛ፤ መንግሥቱን ከዚህ ዓለም ገዢ መልሶ አጸና:: "እግዚአብሔር ነገሠ፤ ክብርንም ለበሰ፤ እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፤ ታጠቀም፤" እርሱ በመስቀል ላይ ነገሠ /መዝ 93÷1/::

በዚህም ምክንያት የጌታችንን ሞት የምናስብበት የተሰዓቱ ሰዓት ጸሎት በውዳሴ፣ በክብር በአምልኮ /በመገዛት/ መዝሙሮች የተሞላ ነው:: በሞቱም ጊዜ ከኃያሉ ጌታ ፊት እንቆ ማለን:: "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም...." እያልን እንዘምርለታለን::

# ከሞቱም በኋላ ኃያል ነበር

ጌታችን ቅድስት ነፍሱን ከለየ በኋላ ያደረገው የመጀመሪያ አምላካዊ ሥራ ዲያብሎስን መጠረቅ ለሺሕ ዓመታትም ማሰር ነው። ጌታችን "ወደ ምድር ታችኛው ክፍል ወረደ " (ኤፌ 4፥9)። ለሙታንም የምሥራቹን ወንጌል ነገረ። በቀኙ ከነበረውም ወንበዴ ጋር ወደ ገነት መራቸው።

ከአዳምና ከሔዋን ውድቀት ጀምሮ ለሺሕ ዓመታት ከተዘጋ በኋላ የገነትን ደጅ የከፈተው የጌታ ሞት ነበር። ሞቶ በታተመ መቃብር ውስጥ እንደገባ ያስቡት የነበረው እርሱ፤ የገነትን ደጅ ከፈተ። የእርሱን የድል መንገድ ሲጠባበቁ ተስፋ አድርገው የሞቱትንም ሁሉ ወደ ገነት መራቸው።

ከጌታ ሞት በኋላ የነበረው ሌላው ድንቅና ማራኪ ታሪክ ኒቆዲሞስ "ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት...." ማለቱና ከታወቀው የመላእክት የሥላሴ መዝሙር የተወሰደውን ቃል ነው። ከቅዱስ መቃብሩ ጐን እንቆማለን። ለጌታችንም በሞቱ "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም....." እንለዋለን። ጌታችን በትንሣኤውም ኃያል ነበር፤ የታተመ መቃብርን ትቶ በተነሣ ፤ ሞትን በማረከ ጊዜ ኃያል ነበር።



www.ethiopianorthodox.org



# ጌታችን ኃይሉን ከዲያብሎስ ሰወረ

ሰዎች ጌታችንን ደካማ አድርገው እንዲያስቡ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንዱ እርሱ ኃይሉን የመሰወሩን ምስጢር አለመረዳታቸው ነው። ይህ ዲያብሎስን ግራ ያጋባው "እውን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውን? እርሱ ነው ወይስ እርሱ አይደለም?" እያለ እጅግ እንዲያደንቅ ያደረገው የትሕትና ሥራው ነበር። ይህ ለመልካም የሆነ ነበር። ዲያብሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነውን እውነታ እንዳይረዳ ክብሩን ሰውሮ ነበር። ዓለም የሚድንበትን መንገድ ሁሉ በሚቻለው ሁሉ ለማሰናከል የሚተጋ፣ ዓለም እንዲድን የማይፈልግ ነውና።

የሚከተሉት ምሳሌዎችም ጌታችን ኃይሉን በመሰወሩ ምክንያት ዲያብሎስ ለገባበት ግራ መጋባት ምስክሮች ናቸው።

ዲያብሎስ ክርስቶስ በነቢዩ ኢሳይያስ ቃል "እነሆ ድንግል በድንግልና ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች" /ኢሳ 7፥14/ ተብሎ እንደተነገረ ከድንግል እንደሚወለድ ያውቅ ነበር። ነቢዩ ከዚህም በተጨማሪ የወልድን ሥልጣን "ሕፃን ተወልዶልናልና፤ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል" በማለት ገልጿልና /ኢሳ 9፥6/።

ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" /ማቴ 16÷14/። ጌታችንም ደቀመዛሙርቱን "እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ" ብሎ ጠየቃቸው። ስምዖን ጴጥሮስም "አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎ መለሰ። ጌታችንም "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ" አለው /ማቴ 16÷17/። ዲያብሎስ ይህንን የማያጠራጥር የማያጠያይቅ ንግግር ሰማ፤ ለራሱም "እርሱ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም" አለ።

ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ‹‹ወደ ኢየሩሳሌም እሔዳለሁ፤ መከራን እቀበላለሁ፤ ሞቼ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ›› ሲላቸው በሰማ ጊዜ ግን የዲያብሎስ ጥርጣሬ ዳግመኛ ተቀሰቀሰ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት መከራ ይቀበል ይሞትም እንደሆነ ሊያስተውል አይችልም ነበርና።

ነገር ግን ክርስቶስ የሰውን ልጅ የሚያድንበት መንገድ ነበር። ዲያብሎስ ግን በጴጥሮስ አንደበት ቃልን አዘጋጀ ጌታንም "አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይድረስብህ" አለው። ጌታችን ግን ወደ ጴጥሮስ ዞሮ "ወደ ኋላዬ ሒድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና" አለው /ማቴ 16÷22/።

ዳግመኛም ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ እንደሚጠበቀው መሲሕ እንደ ንጉሥ ሲቀበሉት ሕፃናትም "ከሕፃናትና ከሚያጠቡ



www.ethiopianorthodox.org



ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ" የሚለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ /መዝ 8÷2/ ሲያመሰግኑት ባየ ጊዜ እርሱ ሊሆን ይችላል ብሎ አሰበ። እንዲሁም በክብሩም ቤተ መቅደሱን አጸዳ። ነገር ግን ጌታችን ወደ ቢታንያ ፊቅ ሲል ባየው ጊዜ መልሶ ተጠራጠረው።

ጌታችን የዲያብሎስን መንግሥት መሻር ጀመረ፤ ለሕዝቡም የጸሐፍት ፈሪሳውያንን ግብዝነት ገለጠ። "እናንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ*" አላቸው /ማቴ 23.1-3/። ሌዋዊ ክህነትንም በወይኑ አትክልት ባለቤትና በገበሬዎቹ ምሳሌ በመናገር ሻረ /ሉቃ 20÷9-19/። ጌታችን ፈሪሳውያንን፣ ሰዱቃውያንንና ሄሮዳውያንን አሳፈረ፤ "ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም" /ማቴ 12÷34/። በዚያ ላይ ዲያብሎስ ጌታችን ለማስያዝ ተዘጋጀ፤ ሤራውም በዕለተ ረቡዕ ተወጠነ።

ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር በዕለተ ሐሙስ ሲያጥብ ዲያብሎስ ተመለከተ። በዚህ ጊዜ ድፍረት ጨመረለት "ይህ እርሱ ክርስቶስ አይደለም" አለ። እንዴት ጌታ አምላክ የሰዎችን እግር ያጥባል! ይሁዳ ከሕብስቱ ቁራሽ በቀመሰ ጊዜ ዲያብሎስ በውስጡ ገባበት ሤራውንም እንዲያውጠነጥን አደረገው /ዮሐ 13÷2/።

ክርስቶስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን ቃሉን /ንግግር/ ሲያደርግ በሰማ ጊዜ መንፈስ ቅዱስንም እንደሚልክላቸው መናገሩን በተረዳ ጊዜ መልሶ መሲሕ እርሱ ነው ብሎ

ሁሉ አንተ ብቻህን ሳለህ ክቡር ነበርክ። የቱም ፍጥረት እንዲያከብርህ የምትሻ አይደለህም፤ አንተ በባሕርይህ በመለኮትህ በሥራህም ሁሉ ክቡር ነህ እንጂ። አንተ "አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" ብለህ እንደተናገርህ ማንም አንተን እንዲያከብርህ የምትሻ አይደለህም /ራእ 22÷13/።

ጌታ ሆይ! እኛ ስናከብርህ የምንጨምርልህ አንዳች አዲስ ነገር የለም፤ ራስህን ዝቅ ዝቅ ባደረግህ ጊዜ እንኳ ብዙ ሁነቶች ክብርህን ያሳያሉ።

በዕለተ ልደትህ ለእረኞች የምሥራችን ባመጡ መላእክት አንደበት ተመስግነሃል /ከብረሃል/። ለአንተም ክብር የሚገባ መባዕ ባመጡልህ ሦስቱ የጥበብ ሰዎች /ሰብአ ሰገል/ ተመስግነሃል፤ ሰግደውልሃልም። ገና በሕፃንነት ወራትህ ወደ ግብጽ በተሰደድህ ጊዜ፣ ጣዖታትም በወደቁ ጊዜ ከበርክ /ኢሳ 19÷1/።

ዮሐንስ መጥምቅም አከበረህ "ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል" አለ /ማር 1÷7-8/። በጥምቀትህ ክብርህ ተገለጠ። መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወደ አንተ በወረደ ጊዜ፣ "የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ ባንተ ደስ ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማይ በተሰማ ጊዜ





ክብርህ ተገለጠ /ሉቃ 3÷22/። ፊትህ እንደ ፀሐይ ባበራ ጊዜ፣ ልብስህም እንደ ብርሃን ነጭ በሆነ ጊዜ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ" በተሰማ ጊዜ በደብረ ታቦር ተራራም ክብርህ ተገለጠ /ማቴ 17÷2/።

በብዙ ተአምራትም ክብርህን ገለጥክ። አጋንንትም ሳይቀር ምስክር ሆኑ። በተራራም ላይ በሰይጣን በተፈተንህ ጊዜ ክብርህን ገለጥክ። ሰይጣንንም ገሠጽከው፤ ትቶህም ሄደ። መላእክትም ሊያገለግሉህ ቀረቡ /ማር 1÷13/። ክብርህን በወርቅ መቅረዞች መካከል ባየ በዮሐንስ ራእይም ተገለጠ።

ፊትህ በሙሉ ኃይሏ እንደወጣች ፀሐይ ያበራ ነበር። ዓይኖችህም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ። ድምፅህም እንደ ብርቱ ፏፏቴ ነበር። ዮሐንስም ባየህ ጊዜ እንደ ሞተ ሆኖ በእግሮችህ ሥር ተደፋ /ራእ 1÷13-17/። በዳግም ምጽአትህም በሰማይ ደመና በክብር ትመጣለህ "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያ ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል" እንደተባለ /ማቴ 25÷31/። "ደመናና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው፤ ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው፤... መብረቆቹ ለዓለም አበሩ፤ ምድር አየችና ተናወጠች" /መዝ 97÷2-5/።



www.ethiopianorthodox.org

# በረከትና ቅድስናም ሁሉ የአንተ ነው

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በስቅለቱ በጆሮዎቹ በሹክሹክታ "በረከትም የአንተ ነው ....." እያልን እንከተለዋለን። መጽሐፍ "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው" ይላልና /ገላ 3÷13/። በዚህም ምክንያት በዚህ መንገድ የሚቀጣ ወንጀለኛ በዚያው ቀን መቀበር ነበረበት። ምድሪቱን እንዳያረክስ በዕፅ ተሰቅሎ ሌሊቱን ሁሉ አይቆይም። በዕፅ የተሰቀለ በእግዚአብሔር የተረገመ /የተቀሰፈ/ ነውና /ዘዳ 21÷22-23/።

ጌታችንም ስለ እኛ በደል /ኃጢአት/ እንደተቀሰፈ/እንደ ተረገጠ/ ሆኖ የሕግን ርግማን ወሰደልን። እኛ ግን እርሱ ከኃ ጢአት የነጻ ቅዱስ እንደሆነ እናውቃለን። ያስወገደልን ርግማ ንም የእኛ ነው። በሕግም መሠረት የኃጢአታችን ደሞዝ ነበርና / ዘዳ 28÷27/። እርሱ በእርግጥም ኃጢአተኛ አይደለም። ኃጢአ ትም አይስማማውም፤ ነገር ግን የሌሎችን ኃጢአት አስወገደ፤ የዓለሙንም ሁሉ። ስለዚህ እርሱ በተሸከመልን በደላችን እየተ ጸጸትን እንከተለዋለን።

ከጥልቅ ሐሳባችንም እርሱን "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት



www.ethiopianorthodox.org



ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም። አማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም። ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ! ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ኃይሌ መከታዬና ረዳቴ ለሆንከው ለአንተ ለአምላኬ ለአማኑኤል ለጌታዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ክብርና ምስጋና ጽናትም ለዘላለሙ የአንተ ናቸው።" እንለዋለን።

በዚህም ርግማን ምክንያት እንዳያረክስ ከሠፈሩ /ቅጽሩ/ አውጥተው ሰቀሉት። ስለዚህ በሰሙነ ሕማማቱ ቅዱስ ጳው ሎስ እንዳዘዘን "ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሠፈሩ ውጪ እንውጣ" /ዕብ 13÷13/ እርሱንም እንከተላለን። ስለ ነቢዩ ሙሴ "ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አሰቧልና" እንደተባለው /ዕብ 11÷26/። ስድቡን /ተግሣጹን/ እንሸከማ ለን።

በዚህም ምክንያት ከኤደን ገነት ተባርሮ እንደወጣው አዳም ከሠፈሩ ውጪ የወሰደንን ኃጢአት እያስታወስን ቤተ ክርስቲያን ከሠፈሩ ከመሠዊያው፣ ከመቅደሱና ከቅድስቱ ውጪ ትሆናለች። ጌታንም ከሠፈሩ ውጪ ተከትለን አንተ ጻድቅ ነህ፣ ክፉዎችስ እኛ ነን፤ እኛ ቅጣትና ርግማን ይገባናል፤ አንተ ግን አይደለህም እንለዋለን። "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ

ነገሥታትን፣ ፈላስፎችን፣ አምልኮ ባዕዳንን ይገጥማሉ፤ ይገዳ ደራሉ፤ ዓለምንም ይሞላሉ ብሎ ያሰበ ማነው! "አንቺ እኅታችን እልፍ አእላፋት ሁኚ፤ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረስ" ባልካት ጊዜ ለእና ታችን ለርብቃ የተሰጣት በረከት የአንተ ነው /ዘፍ 24፥60/።

በእውነት ጌታ ሆይ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም....

ኃጢአት በረከትን ይደብቃል (ያጠፋል) ስለዚህ ኃጢአታችን በተወገደ ጊዜ በረከታችን ተመለሰ። አንተ በፍጹም ርኅራኄ "ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ እባርክሃለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን" /ዘፍ 12፥2/ እንዳልከው ሰውን ወደ ቀደመ መዓርጉ መለስከው።

ጌታ ሆይ! በብዙ ጸጋና ቸርነትም የሰጠኸንን በረከት እንድታ ጸናልን እንለምንሃለን። "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም" ባልክ ጊዜ /ዘፍ 1፥28/ የሰማነው በረከት በሰሙነ ሕማማትህ በስድ ስተኛው ቀን/በቅዳሜ ስዑር/ ይመለስልን። እንግዲህ ነፍሴ እግዚአብ ሔርን ታከብረዋለች፤ በእኔም ውስጥ ያለው ሁሉ የተቀደሰ ስሙን።

"ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን፤
ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
ምስጋናውን ሁሉ አትርሺ" /መዝ 103.1-2/



www.ethiopianorthodox.org



# ልዕልና /አዛዥነትም/ ሁሉ የአንተ ነው

የጌቶች ጌታ የንገሥታት ንጉሥ ነህና ልዕልና የአንተ ነው..." /ራእ 17፥14/ አንተ የዓለምን ዙፋን ብትቃወምም፣ በልባችን በእኛ ውስጥ ባለ መንግሥትህ ነግሠሃል። እነዚያ ልባቸውን የማይሰጡህ እንኳ አንተን ይፈሩሃል።

አንተ ክብርና መፈራት አለህና "አዛዥነት የአንተ ነው" አንተ እንደ ወደድከ ራስህን ትሐትና የዋህ ማድረግ ትችላለህ፤ በትሕትናም ራስህን ትጥላለህ (ትንቃለህ) ይህ ግን የአንተን ክብርና መዓርግ አይቀንሰውም።

ብዙ ጊዜም ትሕትናህ ለጠላቶችህ ይጐዱህና ይወግሩህ ዘንድ ዕድል ሰጣቸው። ነገር ግን አንዳች ሳያደርጉብህ በመካከ ላቸው ታልፋለህ። ማንም ሊጐዳህ አይችልም /ሉቃ 4፥30/። በፈቃድህ ራስህን አሳልፈህ የምትሰጥባት ሰዓቲቱ ከመድረሷ በፊት ሊይዙህ አልቻሉም። አንተን ሊቀርቡህ አልተቻላቸውም። በክርክርም መጽናት አልቻሉም።

አንተ ከእነርሱ ጋር ሳለህ ታናሽ ብላቴና ሆነህ እንኳ በተናገርከው ቃልህ ኃያል ነበርክ። ሰሙህ በእጅጉም ተደነቁ። ሌላው ቀርቶ ዲያብሎስም እንኳ ኃያልና የማትማረክ መሆንህን

በጥልቅ ተረዳ። ትሕትናህ ሲቀርብህ ገፋፋው። አንተ በኃይልህ በገሠጽከው ጊዜ ግን ተሸነፈ። ከአንተም ሸሸ። ንግግሩንም አልጨረሰም። የፈተናውም ፍጻሜ ሆነ።

አንተ በምድር ላይ በተመለስክ ዘመን በጊዜያቱ ሁሉ ኃያል፣ የተከበርክና የተፈራህ ነበርክ። የመስቀሉም ታሪክ የጠላቶችህ ፍርሃት ያስከተለው ምላሽ /ግብረ መልስ/ ነው።

አንተ ከእነርሱ ይልቅ ለሰዎች ልብ የቀረብክ ኃያል መሆንህን ተረድተዋልና። አንተ ሰዎችን ከእነርሱ በላቀ አሳመንክ፤ ስለዚህ ስለ ሥልጣናቸው ፈሩ።

ጌታ ሆይ! በመስቀልህ ጐን እንቆማለን፤ እነዚህ ስድብና ንቀቶች ሕማማት ቢሆኑብህም "ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወእዘዝ እስከ ለዓለም ዓለም..." እያልን እንዘምርልሃለን።



www.ethiopianorthodox.org